# የፌዴራል መንግሥት

# የግዥ መመሪያ

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

ሐምሌ/ 1997 ዓ.ም.

# የመንግሥት ግዥ መመሪያ

## 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ የግዥ ሥርዓትን ለመወሰንና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲውን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 430/97 አንቀጽ 55/2 እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥል ጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 19 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል 1

# ጠቅላላ

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ " የፌዴራል መንግሥት የግዥ መመሪያ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሐረጐች የግዥ ሥርዓትን ለመወሰንና ተቆ ጣጣሪ ኤጀንሲውን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 430/97 የተሰጣቸ ውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. " ዝርዝር " ማለት ዕቃው ወይም አገልግሎቱ ሊያሟላ የሚገባውን ጥራት፣ ዓይነትና ደረጃ የያዘ ሰነድ ነው፡፡

2. " አዋጅ " ማለት የግዥ ሥርዓትን ለመወሰንና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲውን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 430/97 ነው::

## 4. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ አዋጁ ተፈፃሚ በሚሆንበት በማናቸውም የፌዴራል መንግ ሥት ግዥ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

## 5. መርሆዎች

1. ማናቸውም ግዥን ለማስፈፀም የተሰጠ ሥልጣን እንዲሁም የግዥ አፈፃ ፀም የሚከተሉትን ዓላማዎች ግብ ማድረስ ይኖርበታል::

   ሀ. በግዥ አፈፃፀም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም ማስገኘት፣ ይህም ማለት ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ከፍ ብሎ የተገለፀው በእያንዳንዱ ግዥ ውሳኔ መስጠትን ብቻ ሳይሆን የግዥ ዕቅድ የመኖርን አስፈላጊነት ይጨምራል::

   ለ. በአዋጁ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በዜግነት ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች አድልዎ ሊደረግበት አይችልም::

   ሐ. ማናቸውም የግዥ ውሣኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና በእያንዳንዱ ግዥ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልፅ መደረግ አለበት::

መ. ውሣኔዎች እና የተወሰዱ እርምጃዎች የሚያስከትሉት ተጠያቂነት ጥብቅ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡

2. በአዋጁ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቃዎቹ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራዎቹ ጥራትና ዋጋ ተመሳሳይ በሚሆንበት ጊዜ ለአገር ውስጥ ምርቶች እና ወይም ኩባንያዎች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

3. የግዥው ወጪ የሚሸፈነው በውጭ ብድር ወይም እርዳታ በሚሆንበት ጊዜ የግዥው አፈፃፀም በብድሩ ወይም በዕርዳታው ስምምነት መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል 2

# የግዥ ዘዴዎች

## 6. የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች

1. ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስድስት የግዥ ዘዴዎች ተፈቅደዋል፡፡

   ሀ. ግልጽ ጨረታ፣

   ለ. የሁለት ደረጃ ጨረታ፣

   ሐ. የመወዳደሪያ ሃሣብ በመጠየቅ የሚፈፀም ግዥ፣

   መ. ውስን ጨረታ

   ሠ. በዋጋ ማቅረቢያ የሚካሄድ ግዥ፣

   ረ. ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ፣

2. በአዋጁ አንቀጽ 25/2 በተደነገገው መሠረት ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም ግዥ ፈፃሚ አካል በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያት እና ሁኔታዎች የሚያስረዳ ሠነድ መያዝ ይኖርበታል፡፡

## 7. በውስን ጨረታ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለበት፣

በአዋጁ አንቀጽ 26/2 በተደነገገው መሠረት በውስን ጨረታ የግዢ ዘዴ መጠቀም የሚቻለው የሚገዛው ዕቃ፣ አገልግሎት ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ጠቅላላ ዋጋ ከሚከተለው የማይበልጥ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ከብር 1,000,000.00

ለ/ ለዕቃና አገልግሎቶች ከብር 250,000.00

## 8. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ መሟላት ያለበት፣

1. የጅምላ ግዥ የሚኖረውን ጥቅም ለማግኘት ግዥ ፈፃሚ አካላት ግዥን አስቀድመው ማቀድ አለባቸው:: ግዥ ፈፃሚ አካላት ሊታቀድ ያልቻለ አጣዳፊ ለሆነ ሥራ ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ እና ዋጋቸው ከዚህ በታች በተመለከተው ገደብ ውስጥ ይሆናል ተብሎ የሚገመቱ ግዢዎችን ከፀደቀው የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ እስከተቻለ ድረስ ቢያንስ 3 አቅራቢዎችን በማወዳደር በሚከተለው አኳኋን መግዛት ይኖርባቸዋል::

   ሀ. የግዥው መጠን ከብር 5,000.00 በታች ሲሆን፣ ለጨረታ ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ በግዥ ፈፃሚ አካላት የበላይ ኃላፊ ውሣኔ፣

   ለ. የግዥው መጠን ከብር 5001.00 እስከ 40,000.00 ሲሆን፣ የግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ በጨረታ ኮሚቴ የቀረበለትን የውሣኔ ሀሳብ ሲያፀድቅ፣

2. በዚህ አንቀጽ ለመጠቀም ሲባል ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት አይችሉም::

## 9. ከአንድ አቅራቢ ለሚፈፀም ግዥ መሟላት ያለበት፣

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ 27 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈፀም የሚቻለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡፡

ሀ. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 "መ" እና "ሠ" መሠረት በዓይነት እና በዋጋ አንድ የሆኑ ዕቃዎችን፣ የምክር አገልግሎ ቶች እና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን ቀደም ሲል እነዚህን ካቀረበ ተጫራች መግዛት ለግዥ ፈፃሚው አካል ጠቃሚ መሆኑ ሲታመንበት፤ በተጨማሪነት የሚታዘዘው ዕቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም የምክር አገልግሎት ዋጋ ቀደም ሲል ከተገዛው ከ25% /ሀያ አምስት በመቶ/ የማይበልጥ ሆኖ የቀድሞው ግዥ ውል ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ወይም ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ በሚቀጥሉት 6 ወራት ውስጥ የሚፈፀም ሲሆን፣

ለ. ግዥ ፈፃሚው አካል ለሚጠቀምበት ዕቃ የሚያስፈልገው መለዋወጫ የሚገኘው ቀደም ሲል ዕቃውን ከሸጠው አቅራቢ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ. ግዥው ከሌላ አቅራቢ እንዲፈፀም ቢደረግ የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ፈፃሚው አካል ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም አገልግሎት ጋር ተጣጥሞ የማይሄድ መሆኑ በባለሙያ ሲረጋገጥ፣

## 10. ልዩ ሁኔታዎች

1. በዚህ መመሪያ የተመለከተው ቢኖርም ግዢ ፈፃሚ አካላት በግዢ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 100 (አንድ መቶ ብር ) ያልበለጡ ግዢዎችን በቀጥታ ከማናቸውም አቅራቢ

ለመግዛት ይችላሉ:: ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈፀመው ጥቃቅን ግዢ ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር 4,000 (አራት ሺህ ብር ) የሚበልጥ ሊሆን አይችልም::

2. ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡ አቅራቢዎች ማግኘት የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም በጉዞ ወቅት በሚያጋጥሙ ያልተጠበቁ ሁኔታዎች ምክንያት ዋጋቸው ከብር 500 (አምስት መቶ ብር) ያልበለጡ ግዢዎችን ከማናቸውም አቅራቢ መግዛት ይችላሉ:: ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈፀመው ግዢ ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር 6,000 /ስድስት ሺህ ብር/ መብለጥ የለበትም::

# ክፍል 3

## በተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች ግዥ ለመፈፀም በቅደም ተከተል መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች

### 11. ግልፅ ጨረታ

ግዥ ፈፃሚ አካላት በግልፅ ጨረታ ዘዴ ግዥን ለመፈጸም በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሠነድ መጠቀም እና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የቅደም ተከተል አፈፃፀሞች መከተል አለባቸው::

### 11.1 የጨረታ ጥሪ

ሀ. ግዥ ፈፃሚ አካላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 32 /1/ በተመለከተው ሁኔታ በቂ ለሆነ ጊዜ እና አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች የጨረታ ጥሪ ይፋ መደረጉን ማረጋገጥ አለባቸው:: የጨረታው ጥሪ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ቢያንስ አንድ ጊዜ ታትሞ መውጣት አለበት::

ለ. የጨረታው ጥሪ ማስታወቂያ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ሊጨ ምር ይገባል፡፡

1. የጨረታው ጥሪ በማስታወቂያ እንዲወጣ ያደረገው ግዥ ፈፃሚ አካል ስምና አድራሻ፣

2. ግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ ለመሠረዝ መብት ያለው መሆኑን፣

3. የሚቀርበውን ዕቃ ዓይነት፣ብዛት እና ርክክቡ የሚፈፀ ምበትን ቦታ ወይም የግንባታ ሥራዎችን ዓይነት እና የሚከናወንበትን ቦታ ወይም የአገልግሎቱን ዓይነት እና የሚሰጥበትን ቦታ፣

4. የጨረታው ተሳትፎ ዜግነትን ሳይመለከት ለማናቸውም አቅራቢ ክፍት መሆኑን ወይም ለተወሰኑ አገሮች ዜጎች ብቻ የተፈቀደ መሆኑን የሚገልጽ እና ይህም የማይ ለወጥ መሆኑን የሚያረጋግጥ መግለጫ፣

5. የጨረታው ሰነድ የሚገኝበትን አኳኋን እና ቦታ፣

6. የጨረታውን ሰነድ ለመውሰድ ሊከፈል የሚገባውን ዋጋ እና የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና መጠን፣

7. የጨረታውን ሰነድ ለመውሰድ የሚከፈለው ዋጋ በምን አገር ገንዘብ እንደሚከፈል እና የአከፋፈሉን ዘዴ፣

8. የጨረታው ሰነድ የተዘጋጀበትን ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች፣

9. ጨረታው ገቢ የሚደረግበትን ቦታ እና ጨረታው የሚ ቀርብበትን የመጨረሻ ቀን፣

## 11.2 በጨረታ ለመሳተፍ ብቃት ያላቸውን ለመምረጥ የሚደረግ ጥሪ

በጨረታ ሊሳተፉ የሚችሉትን ብቃት ያላቸውን ዕጩ ተወዳዳሪዎች አስቀድሞ ለመምረጥ የሚዘጋጀው ጥሪ እንደግዥው ሁኔታ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11.1/ለ/ የተዘረዘሩትን ማካተት ይኖርበታል::

## 11.3 የጨረታ ሰነድ

ግዥ ፈፃሚ አካላት ለማናቸውም ጨረታ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያካተተ የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀት አለባቸው::

1. የተጫራቾች መመሪያ፣
2. የዕቃው ወይም አገልግሎቱ ዝርዝር፣
3. የዋጋ ሠንጠረዥ የያዘ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ማቅረ ቢያ ቅጽ፣
4. የውል ሁኔታዎች፣

## 11.4 የተጫራቾች መመሪያ

የተጫራቾች መመሪያ እንደግዥው ውል ዓይነት ሊለያይ ቢችልም፣ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል::

ሀ. የአገር ውስጥ ተጫራቾች በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ሊኖራቸው እንደሚገባ፣

ለ. የአገር ውስጥ ተጫራቾች ግብር የመክፈል ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ በግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን የተሰጠ ማስረጃ እና አግባብ ያለው የታደሰ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ እንዳ ለባቸው፣

ሐ. ከወጣው ጨረታ ውስጥ ከብር 100,000.00 በላይ ዋጋ ባለው ግዢ የሚሳተፍ ማንኛውም የአገር ውስጥ ተጫራች በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ እንዳለበት፣

መ. የውጭ አገር ተጫራቾች በሚሆኑበት ጊዜ እንደአግባብነቱ በተቋቋሙበት አገር የተሰጣቸውን የኩባንያ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ማቅረብ እንዳለባቸው፣

ሠ. ተጫራቹ ስለማጭበርበር እና ሙስና፣ (ጉቦ መስጠትን እና መቀበልን ጭምር) በኢትዮጵያ ሕጎች የተደነገገውን የሚያከብር መሆኑን በማረጋገጥ ግዴታ በመግባት ከጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን ቅጽ መፈረም እንዳለበት፣

ረ. ጨረታውን ለማዛባት የሚሞክሩ ተጫራቾች ከጨረታው ውጪ እንደሚሆኑ እና ለወደፊትም በመንግሥት ግዢ እንዳይሳተፉ እንደሚደረግ እና ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደሚወረስ የሚያመለክት መግለጫ፣

ሰ. ማናቸውንም ጨረታ ለመገምገም በሥራ ላይ የሚውሉትን ዘዴዎች፣ ለዚሁ ግምገማ የሚያገለግሉትን መስፈርቶች እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን የነጥብ ድርሻ፣

ሸ. ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ የዕቃውን ዓይነት፣ የአምራቹን ስም፣ የተመረተበትን አገር፣ የሞዴሉን ቁጥር የተመረተበትን ዓመት ሊያጠቃልል እንደሚገባ የሚያመለክት ዝርዝር፣

ቀ. የዕቃዎቹ ናሙናዎች በተጫራቾች እንዲቀርቡ የሚያስፈልጉ ከሆነ ተፈላጊዎቹ ናሙናዎች የሚቀርቡበትንና እንደአስፈላጊነቱ በተጫራ ቾች የሚታዩበትን ጊዜ እና ቦታ እንዲሁም እነዚህ ናሙናዎች በጨረታው ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚመለሱ ወይም ሊመለሱ የማይ ችሉ መሆናቸውን፣

በ. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግ፣ እንዲሁም ከጨረታው ራሳ ቸውን ማግለል እንደማይችሉ የሚያመለክት መግለጫ፣

ተ. የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ እና የሥራ አፈፃፀም ዋስትና እን ዲሁም እነዚህ ዋስትናዎች ፀንተው የሚቆዩበትን ጊዜ፣

ቸ. የጨረታው ማቅረቢያ ጊዜ የሚያበቃበትን እና ጨረታው የሚከፈት በትን ቀን እና ሰዓት፣

ነ. የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲሁም የርክክቡን ቦታና ጊዜ፣

ኘ. ተጫራቾች በሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ ስማቸውን፣ፊርማቸ ውን እና አድራሻቸውን ማስፈር እንዳለባቸው፣

አ. ግዥ ፈፃሚው አካል አሸናፊውን ተጫራች በሚመርጥበት ጊዜ የሚገዛውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ብዛት (መጠን) እንደአስፈላጊነቱ እስከ 20% ( ሃያ በመቶ ) ለመቀነስ ወይም ለመጨመር ስላለው መብት፣

ከ. ጨረታው በአንድ ወይም በሁለት ኢንቨሎኘ የሚቀርብ ስለመሆኑ፣ ስለኢንቨሎፖች አስተሻሸግ፣ አንድ ወጥ የሆኑ ዋናና ቅጂ ሠነዶች መቅረብ እንዳለባቸው፣ የቅጂዎችን ብዛት፣ ሠነዶቹ ሥልጣን ባለው አካል የተፈረመባቸው ሊሆኑ እንደሚገባ እና ማህተም እንደሚያስፈልጋቸው፣ ደጋፊ ማረጋገጫዎች (በአቅራቢነት ስለመመዝገብ፣ ግብር ክፍያ፣ የታደሰ ንግድ ፈቃድ... ወ.ዘ.ተ) ስለሚቀርቡበት ሁኔታ፣ የጨረታ ሣጥኑ የሚገኝበትን ልዩ ቦታ፣

ኸ. ተጫራቾች በጨረታ ሠነዱ ላይ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ለግዥ ፈፃሚው አካል ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን እና የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ለአገር ውስጥ ግዢ ለጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ ከተወሰነው ጊዜ ገደብ 10 ቀን በፊት እንዲሁም ለዓለምአቀፍ ግዢ ለጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ ከተወሰነው ጊዜ ገደብ 21 ቀን በፊት ሊቀርብ እንደሚገባ፣

ወ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 28 (1) በተደነገገው መሠረት የቅድሚያ ክፍያ የሚሰጥ ከሆነ፣ የቅድሚያ ክፍያውን መጠን፣

ዘ. ተጫራቾች በጨረታው የአፈፃፀም ሒደት ቅሬታ ካላቸው በግዥ አዋጁ አንቀጽ 52 እና 53 እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 33 መሠረት አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳላቸው፣

ዠ. ግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ ለመሠረዝ መብት ያለው መሆኑን፣

## 11.5. <u>የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር</u>

ሀ. በማናቸውም ግዥ አፈፃፀም መሠረታዊው ጉዳይ የተጠቃሚውን ፍላጎት የሚያሟላ ዝርዝር ማዘጋጀት ነው:: የዚህ ዓይነቱ ዝርዝር በተለይም በተፈጥሯቸው ውስብስብ እና ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቁ የዕቃና አገልግሎት ግዥዎችን በተመለከተ መሠረታዊ ነው::

ስለሆነም የጠቀሜታ ዝርዝር (ስፔስፊኬሽን) እየተባለ በተጨማሪ የሚታወቀው በተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሆኖ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚፈለገውን ለማሟላት ያላቸውን ተፈ ጥሮ፣የሚያስገኙትን ውጤት፣ በመ/ቤቱ ውስጥ ሊያስገኝ የታሰበውን ጠቀሜታ፣ የሚጠየቀውን የቴክኒክ ብቃት፣የአሠራር ባህርያቸውን እና የታቀደላቸውን ሥራ ለማከናወን ያላቸውን የብቃት ደረጃ የሚያካትት ዝርዝር መግለጫ መዘጋጀት አለበት::

ለ. የተጠቃሚው ፍላጎት (የዕቃው ጠቀሜታ ዝርዝር) መታወቅ ከሌ ሎች መካከል የሚከተሉትን ጥቅሞች ለማግኘት አስፈላጊ ይሆናል::

1. የሚፈለገውን ጠቀሜታ ለማስገኘት ያላቸውን ብቃት እና ወጪ ለተደረገው ገንዘብ ተመጣጣኙን ማስገኘታቸውን ማረጋ ገጥ ያስችላል::

2. ጨረታውን ለማዘጋጀት እና ጨረታው ከወጣ በኋላም ግምገማ ውን ለማከናወን መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ የጠቀሜታ እና የቴክኒክ ዝርዝሮች እንዲኖሩ ይረዳል::

3. የውሉ አንድ ክፍል በመሆን የጨረታ አሸናፊውን የሥራ አፈፃ ፀም ለመቆጣጠር ያስችላል::

ሐ. የሚፈለገው ዕቃ ወይም አገልግሎት ዝርዝር ግዥው እንዲፈፀምለት በሚፈልገው ክፍል መዘጋጀት ያለበት ሲሆን ፤ ከፍተኛ ወጪ በሚጠይቁ እና ውስብስብ በሆኑ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር አዘገጃጀት የግዥ ፈፃሚ አካላት የባለሙያ ድጋፍ መጠቀም አለባቸው::

መ. የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነን አምራች የንግድ ምልክት ወይም አገልግሎት ሰጪ ማመልከት የለበትም:: በመደበኛ አሠራር የጨረታ ሰነድ የተወሰነን የንግድ ምልክት፣ አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ የማይጠቅስ መሆኑን የሚያረጋግጥ መግለጫ መያዝ አለበት:: ሆኖም ግዥው ለተለየ ፕላንት ወይም መሣሪያ የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችን የሚመለከት ሲሆን ወይም የተፈለጉትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ማቅረብ የሚችል አንድ አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ የአምራቹን ወይም የአገልግሎት ሰጪውን ስም በመጥቀስ ወይም " ተመሳሳይ " የሚል ሐረግ እንዲታከል ማድረግ ያስፈልጋል::

ሠ. ግዥ ፈፃሚው አካል የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር በሚያዘጋጅበት ጊዜ የጥራትና ደረጃዎች መዳቢ ባለሥልጣን የሚያወጣቸውን ደረጃዎች በዝርዝሩ ውስጥ ማካተት አለበት፣

ረ. የዕቃና አገልግሉት ዝርዝር የጨረታው ሰነድ አንድ ክፍል መሆን አለበት:: በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ አቅራቢዎች የተሟላና ትክክለኛ የመወዳደሪያ ሃሳብ እንዲያዘጋጁ በሚያስችል ዓይነት ተሟልቶ እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት::

ሰ. ዝርዝር ማዘጋጀት  የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ግዥ ፈፃሚው አካል የዕቃውን ናሙና ማቅረብ ወይም እንዲቀርብ ማድረግ አለ በት፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የሚከተሉት ሁኔታዎች መጠበቅ አለባ ቸው፡፡

1. የሚቀርበው ናሙና በአንድ አምራች ወይም የንግድ ምልክት በተሠራ ዕቃ የተወሰነ መሆን የለበትም፡፡ ከናሙናው ጋር ተመ ሳሳይ የሆነ ሌላ ዕቃ ማቅረብ እንደሚችሉ ተጫራቾች እንዲያ ውቁት ማድረግ ይገባል፡፡

2. ናሙናዎች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት መቅረብ አለባቸው፡፡

3. ተጫራቾች የተሟላ ናሙና በአካል ማቅረብ የማይችሉ  ሲሆን ስለናሙናው ያላቸውን መረጃ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ይህም የናሙ ናውን ፎቶግራፍ ወይም የተገኘውን የናሙና ክፍል መቅረብን ይጨምራል፡፡

4. ተጫራቾች ያቀረቡት  ናሙና በሚመረመርበት  ወቅት በራሱ ተፈጥሮ ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ካሣ አይከፈላቸውም፡፡ ያልጠፉ ወይም ያልተበላሹ ናሙናዎች ከምርመራ በኋላ ለተጫራቾች ተመላሽ ይደረጋሉ፡፡ ተጫራቾች ያቀረቡትን ናሙና የጨረታ ውጤት ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልወ ሰዱ ለመንግሥት በውርስ  ገቢ ይደረጋል፡፡

## 11.6 <u>የጨረታ ሃሣብ ማቅረቢያና የዋጋ ሠንጠረዥ</u>

ግዥ ፈፃሚ አካላት በተጫራቾች የሚሞላ የጨረታ ሀሣብ ማቅረቢያ ቅጽ ማካተት አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የዋጋ ሠንጠረዥ በጨረታው ሰነድ ውስጥ እንዲካተት ማድረግ ይችላሉ፡፡

## 11.7 የውል ሁኔታዎች

1. ማንኛውም ግዥ ፈፃሚ አካል የመደበኛ የጨረታ ሠነዶች አንዱ ክፍል ሆኖ የተዘጋጀውን አጠቃላይ እና ልዩ የውል ሠነድ ረቂቅ የጨረታው ሰነድ አንድ ክፍል አድርጎ ለተጫራቾች መስጠት አለበት።

2. በመደበኛ ጨረታ ሠነድ ላይ በተመለከቱት አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ማሻሻያ ሊደረግባቸው አይችልም። ልዩ ሁኔታዎችን በያዘው የውል ሠነድ ረቂቅ ላይ ግን ማሻሻያ ማድረግ ተፈቅዷል።

3. ማናቸውም ግዢ ፈፃሚ አካል የመደበኛ ጨረታ ሠነዶች አንድ ክፍል የሆነውን አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች እና ስምምነት የተደረገባቸውን ልዩ የውል ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሠነድ ከአቅራቢው ጋር መፈራረም አለበት።

4. በግዢ ፈፃሚው አካል እና በአቅራቢው መካከል ውል ካልተፈረመ በስተቀር የጨረታው አሸናፊ በመገለፁ ብቻ ውል እንደተፈፀመ አይቆጠርም።

5. በአቅራቢው እና በግዢ ፈፃሚው አካል መካከል የሚደረገው ውል አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራውን አጠናቆ ባያስረክብ፣

   ሀ. ርክክብ ባልተፈፀመበት ግዢ ዋጋ ላይ በየቀኑ 0.1% ወይም 1/1000 መቀጫ እንደሚከፍል፣

   ለ. በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን ዋጋ 10% የሚበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ግዢ ፈፃሚው አካል ውሉን የመሠረዝ መብት እንዳለው፣

   ሐ. የውሉ አፈፃፀም መዘግየት በሥራው እንቅስቃሴ ላይ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ግዢ ፈፃሚው አካል የመቀጫው መጠን 10% እስከሚሞላ ድረስ መጠበቅ ሳይገደድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን መሠረዝ እንደሚችል፣

የሚገልፅ አንቀጽ ውሉ እንዲይዝ መደረግ አለበት።

6. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም በአዋጁ አንቀጽ 45 (2) እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተወሰነው መሠረት ለሚከናወኑ ግዢዎች ውል መዋዋል አስፈላጊ አይሆንም፡፡

7. በዋጋ ማቅረቢያ የግዢ ዘዴ ለሚከናወኑ ግዢዎች አቅራቢው የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ /ፕሮፎርማ/ እና ግዢ ፈፃሚው አካል ለአቅራቢው የግዢ ትዕዛዝ የሰጠበት ደብዳቤ እንደውል ስለሚቆጠሩ ተጨማሪ ውል መዋዋል አስፈላጊ አይሆንም፡፡

## 11.8 <u>በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ</u>

የጨረታ ሰነዶችን ይዘት የሚለውጥ ማናቸውም ማሻሻያ በተሻሻለ ተጨማሪ የጨረታ ሠነድነት የጨረታውን ሠነድ ለገዙ ሁሉ በእኩል ጊዜ እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

## 11.9 <u>የጨረታ አከፋፈት</u>

1. ጨረታው የሚከፈተው በጨረታው ጥሪ በተመለከተው ጊዜና ቦታ በግልጽ ይሆናል፡፡ ጨረታው በጨረታ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን መከፈት አለበት፡፡

   ጨረታው፡-

   ሀ. ተጫራቹ ወይም ሕጋዊ ወኪል በተገኙበት ይከፈታል፣ ሆኖም ተጫራቹ በራሱ ምርጫ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ ሳይገኝ መቅረቱ የጨረታውን መከፈት አያስተጓጉልም፣

   ለ. የጨረታ ኮሚቴ አባላት እና የሚቻል እስከሆነ ድረስ የውስጥ ኦዲት ተወካይ ጨረታው ሲከፈት መገኘት አለባቸው፣

2. የጨረታ ኮሚቴው ሰብሳቢ እያንዳንዱ ተጫራች ያቀረበውን የጨረታ ሰነድ ከፍቶ፣ የተጫራቹን ስም፣ ለውሉ ያቀረበውን ዋጋ እና ማናቸውንም ሌሎች ጠቃሚ ነጥቦችን በንባብ ያሰማል፡፡ የጨረታው አከፋፈት ሂደት ቃለ ጉባዔ ይያዛል፡፡ ይህም ቃለ ጉባዔ የተጫራቾቹን ሥም ያቀረቡትን ዋጋ እና ሌሎችንም አስፈላጊ ነጥቦች የሚይዝ ይሆናል፡፡ ቃለ ጉባዔው እና ተጫራቾች ያቀረቡት ዋናው የመጫረቻ ሰነድ በተገኙት የጨረታ ኮሚቴ አባላት ይፈረማል፡፡ ጨረታው በተከፈተበት ጊዜ የተገኙ ተጫራቾች መገኘታቸውን በሚያረጋግጠው ሠነድ ላይ እንዲፈርሙ ይደረጋል፡፡

## 11.10 ከጨረታ ውጪ ስለማድረግ፣

1. ከሚከተሉት ጥፋቶች ውስጥ አንዱን የፈፀመን ተጫራች ግዥ ፈፃሚ አካል ከጨረታው ውጪ ሊያደርግ ይችላል፡፡

   ሀ. የአገሪቱን ሕጎች በተለይም የግዢ ሥርዓትን ለመወሰን እና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲውን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ፣ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብ እና ድንጋጌዎችን ሲጥስ ወይም በጨረታ ሰነድ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ሳያሟላ ሲቀር፣

   ለ. ቀደም ሲል በወጡ ጨረታዎች የገባውን ግዴታ ሳያከብር የቀረ እንደሆነ፣

   ሐ. የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ወይም የውል ማስከበሪያ ያላስያዘ ከሆነ፣

መ. የተለየ አስተያየትን ለማግኘት ወይም ጨረታውን ለማሸነፍ ለማናቸውም ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ መደለያ መስጠቱ ወይም የመደለያ ሀሳብ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣

ሠ. ተወዳዳሪው በጨረታው ሰነድ ላይ የማጭበርበር ተግባር መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣

2. በዚህ ንዑስ አንቀጽ  የተደነገገውን በትክክል ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል ግዢ ፈፃሚ አካላት በአዋጁ አንቀጽ 7 (ቀ) መሠረት የእያንዳንዱን ውል አፈፃፀም የሚያሳዩ መረጃዎችን መያዝ አለባቸው::

## 11.11 ጨረታን ስለመመርመር

1. ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 3 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ግዥ ፈፃሚ አካል ጨረታውን የተሟላ ነው ብሎ ሊቀበል የሚችለው በጨረታው ሰነድ የተዘረዘሩትን ተፈላጊ ነጥቦች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው::

2. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 የተመለከተው ቢኖርም ግዥ ፈፃሚው አካል በምርመራ ወቅት የተገኙ የሒሳብ ስህተቶችን ማረም ይችላል:: እንደዚህ ያሉትን የማስተካከያ ዕርምጃዎች ግዥ ፈፃሚው አካል ባፋጣኝ ለሚመለከተው ተጫራች ማስታወቅ አለበት::

3. በጨረታው ሰነድ ከተዘረዘሩት ባህርይዎች፣ የውል ሁኔታዎች እና ከሌሎች ተፈላጊ ነጥቦች ጋር መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁምነገር ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረውም ግዥ ፈፃሚ አካል ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል::

ሆኖም ማናቸውም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ ተገልጾ በጨረታው ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ እንዲገባ መደረግ አለበት፡፡

4. ማንኛውም የግዥ ፈፃሚ አካል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን መቀበል የለበትም፣

   ሀ. በጨረታው የተወዳደረው አቅራቢ ግዥ ፈፃሚው አካል የሚፈል ገውን አነስተኛውን የጥራት መመዘኛ መስፈርት ያላሟላ በመሆኑ ብቃት የሌለው ሆኖ ሲገኝ፣

   ለ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ቁጥር 2 መሠረት የተደረገውን የሂሳብ ስህተት ማስተካከያ የማይቀበል አቅራቢ ሲሆን፣

   ሐ. ተጫራቹ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ያልተመዘገበ ከሆነ፣

   መ. አግባብ ያለው የታደሰ ንግድ ፈቃድ እና የግብር ግዴታውን የተ ወጣ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ያላቀረበ ከሆነ፣

## 11.12. <u>ጨረታን ስለመገምገምና ስለማወዳደር</u>

1. የግዥ ፈፃሚ አካል አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ የሚከተ ሉትን ዘዴዎች መሠረት በማድረግ ተጫራቾች ያቀረቧቸውን የጨረታ ሰነዶች ቀደም ሲል በጨረታ ሠነዱ ውስጥ በተቀመጠው ዝርዝርና መስፈርት መሠረት መገምገምና ማወዳደር አለባቸው፡፡

2. ተጫራች አሸናፊ የሚሆነው፣

   ሀ. ዕቃዎችን በተመለከተ በዕቃው ለመጠቀም የሚያስፈልገውን ወጪ፣ ዕቃው በሚያገለግልበት ሁኔታ ለመጠበቅ እና ለማ ደስ፣ዕቃውን ለመረከብ የሚወስደው ጊዜ፣የአከፋፈሉን ሁኔታ እና የተሰጠውን ዋስትና፣

ለ. ጨረታውን ያወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል በጨረታው ሰነድ ውስጥ ያሰፈረውን በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ እና በአኃዝ ሊገለጽ የሚችል እንዲሁም በግምገማው ሂደት አንፃራዊ ክብደት የሚሰጠው እና እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ የሚገለጽ መስፈርትን መሠረት በማድረግ በሚካሄድ ግምገማ የተገኘውን ውጤት፣

ሐ. በአዋጁ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በጨረታ ሠነዱ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ካሟሉት መካከል ዝቅተኛ የሆነ ውን የጨረታ ዋጋ (ግዥው በዓለም አቀፍ የጨረታ ዘዴ የሚፈ ፀም ካልሆነ በስተቀር የጨረታው ዋጋ ታክስን ማካተት ይኖርበ ታል።)

መሠረት በማድረግ ይሆናል።

3. የመንግሥት ግዥ ሥርዓትን ለመወሰን እና የግዥ ኤጀንሲን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 430/1997 አንቀጽ 19 በተደነገገው መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለተመረቱ ዕቃዎች እና በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ለሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ልዩ አስተያየት ይደረጋል፣

4. ግዥ ፈፃሚው አካል የጨረታውን አሸናፊ በሚመርጥበት ጊዜ መለኪያው ተለይቶ የሚታወቅ እስከሆነ ድረስ በእያንዳንዱ የዕቃ ወይም አገልግሎት መለኪያ የተሰጠውን የነጠላ ዋጋ ወይም ሌሎች የውል ቃሎች እና ሁኔታዎችን ሳይለውጥ የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ብዛት (መጠን) እስከ 20% ( ሃያ በመቶ) ድረስ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር ይችላል።

## 11.13 <u>የጨረታ ማስከበሪያ</u>

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ግልጽ ጨረታ፣ ውስን ጨረታ የመወዳደሪያ ሃሳብ በመጠየቅ የሚፈጸም ግዢ እና ሁለት ደረጃ ጨረታ የግዥ ዘዴዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ በጨረታው ሰነድ ውስጥ ለእያን ዳንዱ ግዥ የሚጠየቀውን ዋስትና በግልፅ መወሰንና መግለጽ አለባቸው:: የጨረታው ማስከበሪያ በጥሬ ገንዘብ የሚቀርብ ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተፈቀደላቸው የታወቁ ባንኮች የሚሰጥ ዋስትና ሆኖ መጠኑም እንደሚከተለው ይሆናል::

   ሀ. ዋጋቸው ከብር 40,001 እስከ 500,000 ይሆናል ተብለው ለሚገመቱ ግዥዎች ከብር 3000 እስከ 5000፣

   ለ. ዋጋቸው ከብር 500,001 እስከ 1,000,000 ይሆናል ተብለው ለሚገመቱ ግዥዎች ከብር 5001 እስከ 10,000፣

   ሐ. ዋጋቸው ከብር 1,000,001 እስከ 5,000,000 ይሆናል ተብለው ለሚገመቱ ግዥዎች ከብር 10,001 እስከ 50,000፣

   መ. ዋጋቸው ከብር 5,000,000 በላይ ይሆናሉ ተብለው ለሚገመቱ ግዥዎች ከብር 50,001 እስከ 100,000 ፣

2. በዋስትና መልክ የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ እንደተጫራቹ ምርጫ ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የተረጋገጠ ቼክ፣ የሌተር ኦፍ ክሬዲት ወይም የባንክ ዋስትና ሊሆን ይችላል::

3. ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውሉ ከተፈረመ በኋላ የጨረታ ማስከበሪያው ለተሸናፊ ተጨራቾች ወዲያውኑ ይመለሳል፡፡ አሸናፊው ተጫራች ያቀረ በው የጨረታ ማስከበሪያ የሚመለሰው የውል ማስከበሪያውን ለግዥ ፈፃ ሚው አካል ገቢ ካደረገ በኋላ ይሆናል፡፡

## 11.14 <u>የውል ማስከበሪያ</u>

1. በዋጋ ማቅረቢያ ከሚፈፀም ግዥ እና ከኪራይ አገልግሎት ግዥ በስተቀር ለማናቸውም ሌላ የግዥ ውል ግዥ ፈፃሚ አካል የውል ማስከበሪያ መቀበል አለበት፡፡ የጨረታው አሸናፊ በጨረታው ማሸ ነፉ ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ የግዥ ውሉን መፈረም እና ለጨረታ ማስከበሪያ ተቀባይነት እንዳላቸው ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 11.13 በተገለፁት የዋስትና ዓይነቶች መሠረት ክፍያ በሚፈፀምበት የገንዘብ ዓይነት የውሉን ዋጋ 10% በውል ማስከበ ሪያነት ለግዥ ፈፃሚ አካል ማስያዝ አለበት፡፡

2. የውል ማስከበሪያው አቅራቢው በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ በግዥ ፈፃሚው አካል ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ ይውላል፡፡ የደረሰው ጉዳት ከውል ማስከበሪያው በላይ ከሆነ ግዢ ፈፃሚው አካል ልዩነቱን ከአቅራቢው መጠየቅ ይችላል፡፡ የደረሰው ጉዳት ከውል ማስከበሪያው ገንዘብ መጠን በታች ከሆነ ተራፊው ለአቅራቢው ይመለሳል፡፡

3. አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለፀለት ቀን ወይም በግዢው አፈፃ ፀም ላይ አቤቱታ የቀረበ ከሆነ በአቤቱታው ላይ ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ተገቢውን የውል ማስከበሪያ ያላስያዘ እንደሆነ ግዥ ፈፃሚው አካል የጨረታ ማስከበሪያውን የመውረስ መብት ይኖረዋል፡፡

4. በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ግዥ ፈፃሚው አካል በቅድሚያ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በመገምገም በውድድሩ ሁለተኛ የወጣውን ተጫራች አሸናፊ ማድ ረግ ወይም አዲስ ጨረታ ማውጣት ይችላል፡፡

5. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ቁጥር 1 የተመለከተው ቢኖርም፣

ሀ. ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ግዥ ውል ከታወቀ የመድን ድርጅት የሚቀርብ በሁኔታ ላይ የተመሠረተ የውል ማስከበሪያ፣

ለ. የምክር አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የተሠማሩ አቅራቢዎች ለሚሰጡት የምክር አገልግሎት እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት የውል ማስከበሪያ የባለሙያ የካሣ መድን፣

ሐ. የመድን አገልግሎት ግዥ ለመፈፀም በወጣ ጨረታ አሸናፊ የሚሆኑ የመድን ድርጅቶች ለግዥ ፈፃሚ አካላት ለሚሰጡት የመድን ዋስትና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ ያስቀመጡትን ገንዘብ ለውል ማስከበሪያ እንዲሆን ከፈለጉና በቂ መጠባበቂያ ያላቸው መሆኑን ከባንኩ ማረጋገጫ፣

ካቀረቡ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

6. በፍትሀብሔር ሕግ በተደነገገው መሠረት ተጫራቾች የሚያቀርቡት ማናቸውም ዓይነት የዋስትና ሠነድ በሁለት ምስክሮች የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

## 12. በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዢ

በአዋጁ አንቀጽ 30 እና 48 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዢ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ከንዑስ አንቀጽ 11.3 እስከ 11.14 በተመለከተው ሁኔታ ለግልፅ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት ይከተላል፡፡

## 13. የመወዳዳሪያ ሃሳብ በመጠየቅ የሚፈፀም ግዢ

1. የመወዳዳሪያ ሀሳብ በመጠየቅ የሚፈፀም ግዢ በአዋጁ አንቀጽ 28 እና 46 የተደነገገውን እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ከንዑስ አንቀጽ 11.3 እስከ 11.14 በተመለከተው ሁኔታ ለግልፅ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት በመከተል ይፈፀማል፡፡

2. በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም የምክር አገልግሎት ግዢ የሚጠይቀው ወጪ ከብር 200,000 በላይ ከሆነ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚመረጡት በቅድሚያ በውድድሩ ተሳታፊ ለመሆን የሚፈልጉ ሀሳ ባቸውን እንዲገልፁ በጋዜጣ ማስታወቂያ እና የሚቻል እስከሆነ ድረስ በግዢ ፈፃሚው አካል ዌብ-ሳይት ከተጠየቁ በኋላ ይሆናል፡፡

3. ግዢ ፈፃሚ አካላት በመወዳደሪያ ሀሳብ ግዢ መፈፀም የሚችሉት በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መደበኛ የግዢ ሠነድ በመጠቀም ይሆ ናል፡፡

## 14. በውስን ጨረታ የሚፈፀም ግዥ

1. በአዋጁ አንቀጽ 26 በተዘረዘሩ ምክንያቶች ግዥ ፈፃሚው አካል በውስን ጨረታ ዘዴ ለመጠቀም የወሰነ ሲሆን እና በጨረታው ተሳ ታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ በሚሆኑበት ጊዜ

በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ፍትሐዊ በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስቱን ጋብዞ ማወዳደር አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በውስን ጨረታ የሚፈፀም ግዢ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ከንዑስ አንቀጽ 11.3 እስከ 11.14 በተመለከተው ሁኔታ ለግልፅ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

3. ግዥ ፈፃሚ አካላት በጨረታ ሰነዱ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ካሟ ሉት መካከል ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች መምረጥ አለባቸው፡፡

## 15. <u>በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ</u>

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት የዋጋ ማቅረቢያን ብዛት ካላቸው ተወዳዳሪዎች መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የአቅራቢዎቹ ቁጥር ከተቻለ ከሦስት ማነስ የሌለበት ሲሆን፣እነዚህም የሚመረጡት ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ይሆናል፡፡ የመወዳደሪያ ዋጋ እንዲያቀርብ የተጠየቀ እያንዳንዱ አቅ ራቢ ከዕቃው ወይም ከአገልግሎቱ ዋጋ በተጨማሪ እንደትራንስፖ ርት፣መድን፣የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ የመሳሰሉ ወጪዎችን በመወዳደ ሪያ ዋጋ ውስጥ መጨመር ያለበት ወይም የሌለበት መሆኑ ሊገለፅለት ይገባል፡፡

2. እያንዳንዱ አቅራቢ እንዲያቀርብ የሚፈቀድለት አንድ የመወዳደሪያ ዋጋ ብቻ ሲሆን፣ ያቀረበውን ዋጋ መለወጥ አይፈቀድለትም፡፡ አቅራቢው በሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ ላይ በግዥ ፈፃሚው አካል እና በአቅራቢው መካከል ምንም ዓይነት ድርድር ሊደረግ አይችልም፡፡

3. ግዥው የሚፈፀመው የግዥ ፈፃሚ አካል የሚጠይቀውን በማሟላት አነስተኛ የመወዳደሪያ ዋጋ ካቀረበው ተጫራች ነው፡፡

## 16. ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዢ

ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ በአዋጁ አንቀጽ 45 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 በተመለከተው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል::

## 17. ዓለም አቀፍ ጨረታ

1. በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በአዋጁ አንቀጽ 49 እና 50 በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል::

2. በአዋጁ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት በዓለም አቀፍ ግልፅ የጨረታ ዘዴ ግዥ ሊፈፀም የሚችለው የግዥው መጠን፣

   ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ከብር 20,000,000.00 በላይ፣
   ለ/ ለዕቃ ግዢ ከብር 5,000,000.00 በላይ፣
   ሐ/ ለምክር አገልግሎት ከብር 1,000,000.00 በላይ፣
   መ/ ለሌሎች አገልግሎቶች ከብር 3,000,000.00 በላይ፣

   ሲሆን ነው::

3. በዓለምአቀፍ ጨረታ በሚፈፀም የዕቃ ግዢ ተሳታፊ የሚሆኑ ተጫራቾች ራሳቸው የዕቃው አምራቾች ካልሆኑ ከአምራቹ የተሰ ጣቸውን ውክልና ማቅረብ አለባቸው::

# ክፍል 4

## የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚደረግ ግምገማና ውድድር

### 18. የምክር አገልግሎት

#### ሀ/ በጥራት እና በዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ፣

1. የግዥ ፈፃሚ አካላት የምክር አገልግሎት ለመስጠት የሚቀርብ በውን ሃሳብ በሚገመግሙ እና በሚያወዳድሩበት ወቅት እያ ንዳንዱን የቴክኒክ ሃሳብ የሚገመግሙት የሚከተሉትን መስ ፈርቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

   ሀ. ከሚሰጠው ሥራ በተገናኘ አማካሪው ያለውን ልምድ፣
   
   ለ. በሥራ ላይ እንዲውል የቀረበውን የጥናት ዘዴ ደረጃ፣
   
   ሐ. ምክሩ ለግዢ ፈፃሚው አካል የሚያስገኘውን ዕውቀት፣
   
   መ. የውጭ ተወዳዳሪዎች በሚያቀርቧቸው የመወዳደሪያ ሐሳቦች ኢትዮጵያውያን ዜጎች በምክር ሥራው ሂደት በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ፣

2. የቀረበው የቴክኒክ ሃሳብ ብቃት ደረጃ በመቶኛ እንደሚከተለው ይመዘናል፡፡

   ሀ. የአማካሪው ልዩ ልምድ……………………………ከ5 እስከ 10 ነጥብ
   
   ለ. ሥራ ላይ ይውላል ተብሎ የቀረበው የምክር ዘዴ ..… ከ20 ’’ 50 ነጥብ
   
   ሐ. በምክር አገልግሎቱ ለሚሳተፉ ቁልፍ ባለሙያዎች…. ከ30 ’’ 60 ነጥብ
   
   መ. ዕውቀት የማሸጋገር ችሎታ………………………… ከ0 ’’ 10 ነጥብ
   
   ሠ. የኢትዮጵያውን ተሳትፎ …………………………….. ከ0 ’’ 10 ነጥብ

3. ግዢ ፈፃሚ አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ/2/ የተመለከተውን የመነሻና የመድረሻ ነጥብ መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዱ መስፈርት የሚሰጠውን ነጥብ መወሰን የሚገባቸው ሲሆን፣ ጠቅላላ ድምሩ ከ100% መብለጥ የለበትም፡፡

4. በቴክኒክ ብቃት ከመቶ ሰባ (70%) በታች ያገኙ ተወዳዳሪዎች ውድቅ ተደርገው 70% እና ከዚህ ነጥብ በላይ ያገኙት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ይከፈታል፡፡

5. ለመገኘት የፈለጉ አማካሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት የዋጋ ማቅረቢያው በግልፅ ይከፈታል፡፡

6. የምክር አገልግሎት የሚገኘው ከውጭ አማካሪዎች ካልሆነ በስተቀር የአገር ውስጥ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ ለግምገማ ሲባል የአገር ውስጥ ታክስን ይጨምራል፡፡ ከዚህ በላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገር ውስጥ እና የውጭ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ወጪ የመጓጓዣ ዋጋ፣ የትርጉም እና የጽሕፈት ሥራ ወጪን ሊጨምር ይችላል፡፡

7. ዝቅተኛ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ ለዋጋ 100 ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን፣ ሌሎች ተወዳዳሪዎች ግን እንዳቀረቡት ዋጋ ከፍተኛ ላቀረበው አነስተኛ ነጥብ ይሰጣል፡፡

8. የቴክኒክ ግምገማ ከመቶ ሰማንያ (80%) የነጥብ ድርሻ፣ የዋጋ ግምገማ የነጥብ ድርሻ ደግሞ ከመቶ ሃያ (20%) ይሆናል፡፡

9. ለቴክኒክ ብቃት ደረጃ እና ለዋጋ የተሰጡትን ነጥቦች በማዳመር በአጠ ቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው ተወዳዳሪ አሸናፊ ሆኖ ይመረ ጣል::

## ለ. በሚከናወነው ሥራ ጥራት ላይ የተመሠረተ መረጣ፣

የዚህ ዓይነቱ የመረጣ ዘዴ የሚያገለግለው፣

1. አንድ የተወሰነ ማጣቀሻ ሠነድ (TOR) ማዘጋጀት እና ከአማካሪው የሚገኘውን የምክር አገልግሎት ዓይነት ለይቶ ማወቅ በማይቻልበት እና አማካሪው የራሱን የፈጠራ ችሎታ ተጠቅሞ ሀሳብ እንዲያቀርብ የሚጠበቅ በሚሆንበት ጊዜ፣
2. ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን አማካሪዎች ማግኘት አስፈላጊ በሚሆንባ ቸው እና የወደፊት ውጤታቸው አሳሳቢ የሚሆን ከፍተኛ ጉዳዮች ሲሆኑ፣
3. የምክር አገልግሎቱ በተለያዩ አማራጭ መንገዶች ሊቀርብ የሚችል በመሆኑ ምክንያት የሚቀርቡትን ሀሳቦች ማወዳደር አስቸጋሪ ሲሆን፣

## ሐ. በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ፣

የዚህ ዓይነቱ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው የሚፈለገው የምክር አገልግሎት ውስብስብነት የሌለው እና በትክክል ሊገለፅ የሚችል ሲሆን፣ እንዲሁም ለዚሁ ተግባር የተፈቀደው በጀት ጣሪያ ያለው ከሆነ ነው::

### መ. በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ፣

የዚህ ዓይነቱ የመረጣ ዘዴ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ለአማካሪው የሚሰጠው ሥራ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት የመወዳደሪያ ሀሳቦችን ለማዘጋጀት እና ለመገምገም የሚያስፈልገው ጊዜና ወጪ ከሥራው ጋር የማይመጣጠን ሲሆን ነው:: ሆኖም ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው የምክር አገልግሎቱ ወጪ ከብር 50,000 የማይበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው::

## 19. ሌሎች አገልግሎቶች፣

1. እንደቁፋሮ፣ የአየር ሁኔታ ጥናት፣ የግዥ ወኪሎች ወዘተ... የመሳሰሉትን አገልግሎት የሚሰጡ አቅራቢዎች በሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ ላይ ግምገማ የሚካሔደው በጨረታው ሰነድ በተገለጸው መስፈርት መሠረት ይሆናል። ለማናቸውም ጨረታ እንደሚከተለው ክብደት የተሰጣቸው ሦስት መስፈርቶች ይኖራሉ:-

   ሀ. **ለቴክኒክ ባህርያት፣** የሚሰጠው ክብደት ከ50 - 60 % ሲሆን፣ እነዚህ ባህሪያት አስፈላጊ ቢሆኑና ቢኖሩ ይበጃሉ በተባሉ መካከል ለመለየት ያስችላሉ::

   ለ. **ለመወዳደሪያ ዋጋ፣** የሚሰጠው ክብደት ከ30-40% ይሆናል::

   ሐ. **እንደማጠናቀቂያ ጊዜ፣** የአከፋፈል ሁኔታ፣አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችል ዝግጅት፣ የተቋራጩ የሥራ አውታሮች ለመሳሰሉት ገጽታዎች የሚሰጠው ክብደት ከ10-20% ይሆናል::

# ክፍል 5

# ሥልጣን እና ኃላፊነት

## 20. የግዥ ፈፃሚ አካል ኃላፊነት እና ስልጣን

የግዥ ፈፃሚ አካል የበላይ ኃላፊ በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች እና ሥልጣን ይኖሩታል፡፡

1. በበላይነት የሚመራው ግዥ ፈፃሚ አካል በዕቃና አገልግሎት ግዥ አፈፃፀም ወጪ ላደረገው ገንዘብ ተመጣጣኙን ማግኘቱን ማረጋገጥ፣
2. ከጨረታ ኮሚቴው የሚቀርብለትን ማናቸውንም ሃሳብ መርምሮ ውሣኔ የመስጠት፣
3. የጨረታውን ውጤት የጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች እና በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑት ለሁሉም ተጫራቾች በእኩል ጊዜ በጽሑፍ የመግለፅ፤ (ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚገለፀው የተሸነፉበትን ምክንያት እና አሸናፊ የሆነውን ተጫራች የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡)
4. በንግድ ሥራ ውስጥ በሚስጥርነት ሊጠበቅ የሚገባውን በተጫራቾች የቀረበውን መረጃ ለሌላ አለመግለፅ፣
5. በግዥ ኤጀንሲው የሚጠየቁ ወቅታዊ የግዥ መረጃዎችን እና ሪፖር ቶችን ለኤጀንሲው የመስጠት፣

## 21. የጨረታ ኮሚቴ አሰያየም

1. የጨረታ ኮሚቴ የሚሰየመው በግዥ ፈፃሚ አካል የበላይ ኃላፊ ሆኖ ኮሚቴው ሰብሳቢውን እና ፀሐፊውን ጨምሮ አምስት አባላት ይኖሩ ታል፡፡

2. የጨረታ ኮሚቴ አባላት ሆነው ሊመረጡ የሚችሉት በመልካም ሥነ-ምግባር የሚታወቁ፣ በዲሲፒሊን ጥፋት ተከሰው እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና ግዥ ለመፈፀም የተሻለ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ሠራተኞች መሆን አለባቸው:: የሚቻል እስከሆነ ድረስ አምስቱ አባላት ከግዥ ፈፃሚ አካል የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ይሆናሉ::

3. የግዥ ፈፃሚ አካል የውስጥ ኦዲት የሚቻል እስከሆነ ድረስ በኮሚቴው ውስጥ በታዛቢነት ይገኛል::

4. የጨረታ ኮሚቴ ሊሰበሰብ የሚችለው ከአባላቱ ቢያንስ ሦስቱ ሲገኙ ነው:: ውሣኔ የሚተላለፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል:: ይሁን እንጂ ድምፁ እኩል ለእኩል በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል:: በሃሳብ የተለየ አባል ሲኖር የተለየበት ምክንያት በቃለ ጉባዔው እንዲሰፍር ይደረጋል::

5. የጨረታ ኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን አስገዳጅ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ሁለት ዓመት ይሆናል:: ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የጨረታ ኮሚቴ አባል የነበረ ሠራተኛ በድጋሚ ሊሰየም ይችላል::

## 22. <u>የጨረታ ኮሚቴ ኃላፊነት</u>

የጨረታ ኮሚቴ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል::

1. የግዥ ሥራ ክፍሉን በማማከር የግዥ ዘዴን የመምረጥ፣
2. በአዋጁና በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሠረት የአቅራቢዎችን የመወዳደሪያ ሃሣቦች መርምሮ ለግዥ ፈፃሚ አካል የበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሃሣብ የማቅረብ፣

3. አግባብ ሆኖ ሲገኝ የሚከተሉት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሀሳብ የማ ቅረብ፣

ሀ. ተጫራቾች በበቂ ምክንያት አስደግፈው የጨረታ ጊዜ እንዲራዘም የሚያቀርቡትን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ጊዜው እንዲራዘም ሃሣብ ሊያቀርብ ይችላል:: ይሁን እንጂ ከሚሰጡት ምክንያቶች ውስጥ የሚከተሉት ተቀባይነት አይኖ ራቸውም::

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 32 መሠረት ለጨረታ ማቅረቢያ በተፈቀደው ጊዜ ውስጥ የጨረታውን የመወዳደሪያ ሠነድ ለማዘጋጀት አለመቻል፣

2. በመገናኛ ችግር ምክንያት ጨረታው ስለመውጣቱ ያለ መስማት፣

ለ. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 11/10/ መሠረት ማናቸውንም ተጫ ራች ከጨረታ ውጪ ማድረግ፣

ሐ. ለመ/ቤቱ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጨረታውን የመሠረዝ፣

4. የጨረታ ኮሚቴው የማናቸውንም ጨረታ ቴክኒካዊ ሁኔታ ለመመ ርመር የቴክኒክ ባለሙያዎችን መጠቀም ይችላል:: እነዚህ ባለሙያ ዎች ከሚከተሉት ማናቸውም ሊሆኑ ይችላሉ::

ሀ. ጨረታውን ካወጣው ግዥ ፈፃሚ አካል፣

ለ. ከሌሎች ግዥ ፈፃሚ አካላት፣

ሐ. በሚመረመሩት ጉዳዮች ልዩ ሙያ ያለው አማካሪ ወይም የግል ኩባንያ፣(ሆኖም በሥራው የሚሳተፍ አማካሪ ወይም የግል ኩባንያ ሊከናወን ከታሰበው ግዥ ጋር ግንኙነት የሌለው መሆን አለበት።)

5. የጨረታ ኮሚቴ ሊቀመንበር እና ፀሐፊ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያ ያዘው ዕዝል 1 እና 2 የተመለከተው ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸ ዋል።

## 23. ተቀባይነት ባገኘ የአቅራቢዎች ዝርዝር ስለመጠቀም

1. የአቅራቢዎችን ዝርዝር የማቋቋም ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

   ሀ. የግዥ ፈፃሚ አካላት ተገቢ የሆኑ አቅራቢዎችን በአፋጣኝ እንዲለዩ ለማስቻል፣

   ለ. ብቃት ያላቸው አቅራቢዎችን በመምረጥ ረገድ የሚደረገውን ማጣ ራት ለማጠናከር፣

   ሐ. ወጪ ለተደረገው ገንዘብ ተመጣጣኙን ማስገኘት እንዲቻል ከአቅራቢዎች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ከተገኘ ልምድ የተለያዩ ዘዴዎችን ለማዳበር፣

2. በመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ መመዝገብ ቅድመ ሁኔታ ነው። ስለሆነም በመንግሥት ግዥ ውስጥ ለመሳተፍ የሚፈልጉ የአገር ውስጥ ዕቃ አቅራቢዎች እና ምክር አገልግሎት ሰጪዎች ከግዥ ኤጀንሲ እንዲሁም ለኮንስትራክሽን ሥራዎች እና ለተሽከርካሪ አቅርቦት ከመሠረተ ልማት ሚኒስቴር፣ (ከዚህ በኋላ " አግባብ ያለው ባለሥልጣን " እየተባሉ ከሚጠሩት አካላት) የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርባቸዋል።

3. የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የሚጠይቅ ማናቸውም አቅራቢ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላትና የሚከተሉትን በማያያዝ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

   ሀ. የንግድ ፈቃድ፣

   ለ. ታክስ መክፈሉን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት፣

   ሐ. የምክር አገልግሎት በመስጠት የተሠማራ አቅራቢ ከሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" ከተገለፀው በተጨማሪ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፣

   መ. በግንባታ ዘርፍ ሥራ ላይ የተሠማራ አቅራቢ ከሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" ከተገለፀው በተጨማሪ የምዝ ገባ ደረጃውን መስፈርት የሚያሟላ የመሣሪያና የሰው ኃይል ዝግጅት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች፣

4. አግባብ ላለው ባለሥልጣን የምዝገባ ጥያቄ ሲቀርብ፣ ባለሥልጣኑ የቀረበው ማመልከቻ እና መረጃው መሟላቱን በማረጋገጥ የምስክር ወረቀቱን ከሦስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መስጠት አለበት፡፡

5. አቅራቢው በግዥው ውል መሠረት ግዴታውን ሳይፈፅም ሲቀር ወይም ፕሮፎርማ እንዲሰጥ ሲጠየቅ ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ለማቅረብ እየቻለ ፕሮፎርማ ያልሰጠ ወይም ዕቃውን ወይም አገልግ ሎቱን ለመስጠት የማይችል መሆኑን ለማረጋገጥ ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ስሙንና ደጋፊ ማስረጃዎችን የግዥ ፈፃሚ አካላት ለግዥ ኤጀንሲ መላክ አለባቸው፡፡

6. የግዥ ኤጀንሲው፣

ሀ. አገልግሎቱን ሳያጠናቅቅ የቀረ ወይም አሸናፊ መሆኑ በተገለፀለት በ15 ቀን ውስጥ የግዥውን ውል ያልፈረመ አቅራቢ እንደጥፋቱ ክብደት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ወይም ከአቅራቢዎች ዝርዝር እንዲሰረዝ ሊያደርግ ይችላል፣

ለ. የግዥ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በቀረ በለት ሪፖርት ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ለአቅራቢው የቀረ በበትን የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚገልፅ ማስታወቂያ መላክ ይኖር በታል:: አቅራቢው ማስታወቂያው በደረሰው በ5 ቀን ውስጥ በጉዳዩ ላይ ያለውን አስተያየት እና መረጃ ለግዥ ኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል::

ሐ. የግዥ ፈፃሚ አካላት ለሚፈጽሙት ግዥ ኘሮፎርማ እንዲሰጥ ሲጠየቅ ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ሊያቀርብ እየቻለ ፕሮ ፎርማ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም ዕቃው የሌለው ወይም አገልግሎቱን ለመስጠት የማይችል ከሆነ ይህንኑ በኘሮፎርማ መጠ የቂያው ሰነድ ላይ ለማረጋገጥ ፈቃደኛ አለመሆኑ ሲረጋገጥ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው ከማድረግ ጀምሮ ከአቅራቢዎች ዝርዝር እስከመሠረዝ የሚደርስ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል::

7. የግዥ ኤጀንሲው ከሚከተሉት በማንኛውም ምክንያት የምስክር ወረቀቱን ሊሠርዝ ይችላል::

ሀ. የምስክር ወረቀቱ የተገኘው የሀሰት መረጃን በማቅረብ መሆኑ ሲረ ጋገጥ፣

ለ. የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ጥያቄ ባቀረበበት ወቅት የሰጣቸው መረጃዎች የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ እንዲቆይ በማያስችል ሁኔታ ተለውጠው ሲገኙ ለምሳሌ አቅራቢው የንግድ ፈቃዱ የተሠረዘበት ወይም የታክስ ግዴታውን መወጣት ሲያቋርጥ ወይም የማጭበርበር ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፣

ሐ. አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩትን ጥፋቶች ፈፅሞ ሲገኝ፣

መ. አቅራቢው በዝርዝሩ መሠረት ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ፣

8. ከዚህ በላይ ባሉት አንቀጾች መሠረት የግዥ ኤጀንሲው የአቅራቢውን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሲሰርዝ ይህንኑ ውሳኔ ለአቅራቢው እና ለግዥ ፈፃሚ አካላት ማስታወቅ አለበት፡፡ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ መሠረዝ ውሣኔ የሚፀናው በማስታወቂያው ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

9. በአቅራቢዎች ዝርዝር ባይመዘገቡም በስራቸው አጋጣሚ ዕቃ ወይም አገልግሎት በመሸጥ ተግባር ላይ ከተሰማሩ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/89 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 13 እንደተደነገገው በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመንግሥት በጀት ከሚተዳደሩ የመንግሥት መ/ቤቶች የግዥ አፈፃፀም ስርዓቶችን በጠበቀ መልኩ ግዥ መፈፀም ይችላል፡፡

10. ከአዲስ አበባ ውጪ የሚገኙ የፌዴራል መ/ቤት ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በሚኖሩበት አካባቢ ለሚፈፅሙት ግዥ የተመዘገበ አቅራቢ ማግኘት አለመቻላቸውን ካረጋገጡ ያልተመዘገቡ አቅራቢዎችን አወዳድረው ግዥ መፈፀም ይችላሉ፡፡

## 24. ከግዥ ፈፃሚ አካላት የሚቀርቡ መደበኛ ያልሆኑ የግዥ ሃሳቦችን ስለመመርመር

የግዥ ፈፃሚ አካላት በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሊጠብቅ ያልቻለ ( መደበኛ ያልሆነ ግዥ ) መፈፀም የሚችሉት በግዥ አዋጁ አን ቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 5 በተደነገገው መሠረት ለግዥ ኤጀንሲው ጥያቄ ያቸውን አቅርበው ሲፈቅድላቸው ብቻ ነው:: ከጥያቄው ጋርም ተገቢውን መግለጫና ሌሎች ደጋፊ ሠነዶች ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

## 25. የተሽከርካሪ ግዥ አፈፃፀም

1. የተሽከርካሪ ግዥ የሚፈጸመው የመንግሥትን ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፍላጎት በማጠቃለል ይሆናል::
2. የፌዴራል መ/ቤቶችን የተሽከርካሪ ግዥ አጠቃሎ የሚገዛው የፌዴራል መንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው::
3. የግዥ ፈፃሚ አካላት ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፍላጎታቸውን በየዓመቱ ከሐምሌ 30 ቀን በፊት ለፌዴራል መንገድ ትራንስፖርት ባለሥል ጣን ማቅረብ አለባቸው::
4. የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን የግዥውን ጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል፣ ተጫራቾችን ይጋብዛል፣ የሚደርሱትን የመወዳደሪያ

ይገመግማል፣ አሸናፊውን ተጫራች ይመርጣል፣ የጨረታ ውድድ ሩን ውጤት ለሁሉም ተወዳዳሪዎች በደብዳቤ ያሳውቃል፣ በውድድር ውጤት ላይ የተቃውሞ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ከአቅራቢው ጋር የውል ማዕቀፍ ይፈርማል:: የሚመለከተው የግዥ ፈፃሚ አካል ዝርዝር ውሉን መፈፀም እንዲችል የጨረታውን አሸናፊ፣ ለተሽከርካሪው የተዘጋጀውን ዝርዝር እና የመሸጫ ዋጋ ያሳውቀዋል::

5. የግዥ ፈፃሚ አካል የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ባስተላለፈ ለት መሠረት ዝርዝር ውል በመዋዋልና የተሽከርካሪውን ዋጋ በመክ ፈል የገዛውን ተሽከርካሪ ይረከባል::

6. የግዥ ፈፃሚ አካል የበላይ ኃላፊ አስቸኳይ ሁኔታ በማጋጠሙ ምክንያት የተሽከርካሪው ግዥ መዘግየት በመ/ቤቱ ሥራ ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል መሆኑን ሲያምንበት እና ለመንግሥት ግዥ ኤጀንሲ አቅርቦ ሲፈቀድለት ስለዝርዝር አፈፃፀሙ የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣንን ሃሳብ በመጠየቅ ግዥውን በራሱ ሊፈ ጽም ይችላል::

## 26. የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ክፍያ የምስክር ወረቀት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11.14 /1/ ከተመለከተው በተጨማሪ ለማናቸ ውም የግንባታ ዘርፍ ሥራ በክፍያ ምስክር ወረቀት መሠረት ከሚፈ ፀመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለሥራ ጥራት ዋስትና እንዲሆን 5% (አምስት በመቶ) በመያዣ መልክ (Retention) ተቀንሶ ይያዛል::

2. የግንባታው ሥራ ሲጠናቀቅና ጊዜያዊ ርክክብ ሲደረግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከተያዘው ገንዘብ ላይ 50% (ሃምሣ በመቶ) ለሥራ ተቋራጩ ይለቀቃል:: ቀሪው 50% (ሃምሣ በመቶ) ለአንድ ዓመት የጥገና ጊዜ ተይዞ ይቆያል:: ሆኖም የሥራ ተቋራጩ ለ12 ወራት የሚቆይ በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ ዋስትና ካቀረበ የተያዘው ገንዘብ ሊለቀቅለት ይችላል::

3. አማካሪ መሐንዲሱ የክፍያ ምስክር ወረቀት ከሥራ ተቋራጩ ተዘጋጅቶ በቀረበለት በ7 (ሰባት) ቀናት ውስጥ የምርመራውን ሥራ ማጠናቀቅ ይኖርበታል::

4. የክፍያ የምስክር ወረቀት በአማካሪ መሐንዲሱ ተረጋግጦ በቀረበ በ14 (አሥራ አራት) ቀናት ውስጥ ግዥ ፈፃሚው አካል ተገቢውን ክፍያ ለሥራ ተቋራጩ መፈፀም አለበት::

5. አማካሪ መሐንዲሱ የክፍያ ምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ከቀረበለት በኋላ ያለበቂ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከተጠቀሰው ጊዜ ያሳለፈ እንደሆነ በመዘግየቱ ምክንያት ተቋራጩ በግዥ ፈፃሚው አካል ላይ ለሚያቀርበው ማንኛውም ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ አማካሪ መሐንዲሱ ኃላፊነት ይኖርበታል:: ሆኖም የአማካሪ መሐንዲሱ ኃላፊነት ለአገልግሎቱ ከሚከፈለው ዋጋ ሊበልጥ አይችልም::

6. ግዥ ፈፃሚው አካል ያለ በቂ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በአማካሪ መሐንዲሱ በቀረበለት ማረጋገጫ መሠረት ክፍያ ባይፈጽም ተቋራጩ በውሉ መሠረት ለሚያቀርበው ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ ኃላፊነት ይኖረዋል::

## 27. ለግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ግዥ አፈፃፀም ስለሚደረግ የቴክኒክ ድጋፍ፣

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 (እንደተሻሻለ) በተደነገገው መሠረት በግዥ ፈፃሚ አካላት የሚከና ወን የግንባታ ዘርፍ ሥራ በተገባው ውል መሠረት የጥራት ደረ ጃው፣ የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚ ያስችል ቁጥጥር እንዲኖር የማድረግና በበላይነት የመቆጣጠር ኃላ ፊነት የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

2. የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር ስለግንባታ ዘርፍ ሥራ ግዥ አፈፃፀም በግዥ ፈፃሚ አካላት ሲጠየቅ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3. ግዥ ፈፃሚ አካላት የግንባታ ዘርፍ ሥራ ግዥ ሲፈጽሙ ከመሠረተ ልማት ሚኒስቴር የቴክኒክ ድጋፍ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

# ክፍል 6

# ልዩ ልዩ

## 28. የቅድሚያ ክፍያ

1. በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም በማንኛውም ሁኔታ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ 30% (ሠላሣ በመቶ) በላይ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ አይችልም፡፡ የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠንም በተጫራቾች መመሪያ ላይ መገለፅ ይኖርበታል፡፡

2. አቅራቢዎች በውሉ መሠረት ከሚጠይቁት የቅድሚያ ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንደአቅራቢው ምርጫ ከታወቀ ባንክ የሚሰጥ የተረጋገጠ ቼክ (C.P.O.) ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከተው ቢኖርም የአገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ፣ የማይሻር እና ያለተጨማሪ ስነ-ስርዓት በመጠየቁ ብቻ ተከፋይ የሚ ሆን ወይም በሁኔታ ላይ የተመሠረተ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ከታ ወቀ የመድን ድርጅት ሊያቀርቡ ይችላሉ።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ለግንባታ ዘርፍ ሥራ በተደ ረገ ውል መሠረት ለሚፈፀም የቅድሚያ ክፍያ የቀረበው ዋስትና በሁ ኔታ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፤ ውል ሰጪው ግዥ ፈፃሚ አካል እና ውል ተቀባይ የሆነው ሥራ ተቋራጭ የቅድሚያ ክፍያውን አፈፃፀም በሚመለከት የተለየ ውል መዋዋል አለባቸው። ውሉም ከሌሎች መካከል፣

   ሀ. በውሉ መሠረት ለሥራ ተቋራጩ የሚፈፀመው የቅድሚያ ክፍያ ለዚሁ ዓላማ በሥራ ተቋራጩ ስም በሚከፈት የተለየ የባንክ ሂሣብ ውስጥ እንደሚቀመጥ፣

   ለ. በዚህ የባንክ ሂሣብ ውስጥ የተቀመጠው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ወጪ ሊደረግ የሚችለው በግዥ ፈፃሚው አካል ተወካይ እና በሥራ ተቋራጩ የጣምራ ፊርማ እንደሚሆን፣

ሐ. በባንክ ሂሣቡ ከተቀመጠው ገንዘብ ላይ ለሥራ ተቋራጩ ክፍያ የሚፈፀመው ቀደም ሲል በወሰደው ገንዘብ ተገቢውን ሥራ የሠራ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ፣

መ. በቅድሚያ ክፍያ መልክ የሚወሰደው ገንዘብ ለማሽነሪዎች መግዣ ሊውል እንደማይችል፣

የሚገልጹ አንቀጾችን የሚይዝ መሆን አለበት::

## 29. ልዩ አስተያየት፣

1. ማናቸውም ዕቃ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተመረተ ተቆጥሮ በጨረታ ግምገማ ወቅት በአዋጁ በተደነገገው መሠረት እስከ 15% ልዩ አስተያየት ሊደረግለት የሚችለው ከዋጋው 20% /ሃያ በመቶ/ በኢት ዮጵያ ውስጥ የታከለ ዋጋ መሆኑን የሚያስረዳ በታወቀ ኦዲተር የተረጋገጠ መረጃ ሲያቀርብ ይሆናል::

2. ማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ሥራ በአዋጁ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው፣

   ሀ. ኩባንያው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ እና ዋና መ/ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣

   ለ. ከኩባንያው አክሲዮን ወይም የካፒታል ድርሻ አብዛኛው በኢትዮ ጵያውያን የተያዘ ከሆነ፣

   ሐ. ከኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል አብዛኛው ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣

   መ. ከኩባንያው ቁልፍ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ 50% ኢትዮጵ ያውያን ከሆኑ፣

ነው::

3. የጨረታ ኮሚቴ ተጫራቾች ያቀረቡትን የጨረታ ሠነድ ከመረመረ በኋላ ተፈላጊውን የሚያሟሉ ሆነው የተገኙትን ተጫራቾች በሁለት ምድብ ይመድባል:: በዚህም መሠረት አስተያየት የሚደረግላቸው የአ ገር ውስጥ ተጫራቾች በአንደኛው ምድብ ሌሎች ተጫራቾች ደግሞ በሁለተኛው ምድብ ይመደባሉ:: የጨረታው ግምገማ በሚደረግበት ጊዜም በሁለተኛው ምድብ ውስጥ የሚገኙ ተጫራቾች ባቀረቡት የመጫረቻ ዋጋ ላይ የተወሰነው የልዩ አስተያየት መቶኛ እንዲደ መርበት ይደረጋል::

4. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም " የታከለ ዋጋ " ማለት ከጠቅላላ ወጪ ላይ ከውጭ አገር ለሚመጡ ጥሬ ዕቃዎች እና ሌሎች አቅርቦቶች እን ዲሁም ከውጭ አገር ለተገኘ አገልግሎት የተደረገ ወጪ ተቀንሶ የሚቀረው ወጪ ሲሆን፣ በምርት ላይ የሚከፈሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን አይጨምርም::

## 30. የሙያ ሥነ-ምግባር

ከግዢ ጋር በተያያዘ ተግባር ላይ የተሰማሩ የመንግሥት ሠራተኞች ሥል ጣናቸውን ወይም የሥራ ደረጃቸውን ለማናቸውም ዓይነት የግል ጥቅም ማዋል የለባቸውም::

በተለይም:-

ሀ. ከግል ጥቅማቸው ጋር የተያያዘ እና ኃላፊነታቸውን በትክክል እንዳይወጡ የማድረግ ውጤት ያለው ወይም የዚህ ዓይነቱ ውጤት ሊኖረው የሚችልን ማናቸውም ሁኔታ ለጨረታ ኮሚቴው በግልጽ ማሳወቅ አለባቸው::

ለ. ስጦታ ወይም መስተንግዶ መቀበል የለባቸውም፣

ሐ. በሥራ አጋጣሚ የሚያገኟቸውን እና በንግዱ ሥራ ላይ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ መረጃዎችን በሚስጥር መያዝ አለባቸው::

## 31. ከአቅራቢዎች ጋር ስለሚደረግ ውይይት

1. በግዥ ሂደት በማናቸውም ደረጃ ከአቅራቢዎች ጋር ውይይት ሊደረግ የሚችለው የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም ብቻ ይሆናል:: በግዥ ፈፃሚው አካል እና በአቅራቢዎች መካከል የሚደረጉ ውይይቶች በሁለት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ይሆናሉ::

እነዚህም:-

ሀ. በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ለመወያየት፣

ለ. የሁለት ደረጃ ጨረታ በሚሆንበት ጊዜ ጨረታው በሚያካ ትታቸው የግዢ ዓይነቶች ላይ ድርድር ለማድረግ፣

2. በጨረታው ሰነድ ላይ በግልፅ ስላልተመለከቱ ጉዳዮች የግዥ ፈፃሚው አካል ማብራሪያ መስጠት አለበት:: አቅራቢዎች የተፈለገውን ግዢ ዓይነት መረዳት የሚያስቸግራቸው በሚሆንበት ጊዜ ጨረታውን ያወ ጣው የግዥ ፈፃሚ አካል ግልፅ ሊያደርግላቸው ይገባል:: ጨረታውን ያወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል በጨረታው የተሳተፉ አቅራቢዎች ሁሉ ተጨማሪው ማብራሪያ የደረሳቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተፈቀደው መሠረት ካልሆነ በስተቀር፣

ሀ. ጨረታው ከተዘጋ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ለውጥ እንዲያደርጉ መጠየቅ ወይም መፍቀድ አይቻልም::

ለ. ጨረታውን ያወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል ጨረታው ከተከፈተ በኋላ የመወዳደሪያ ሃሳቡን ለመገምገም በሚያስችሉ ነጥቦች ላይ ማብራሪያ ከመጠየቅ በስተቀር ተጫራቾች ካቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ውስጥ ዋጋን ወይም ሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን እንዲለውጡ መጠየቅ ወይም መፍቀድ የለበትም::

ሐ. ስለጨረታው የሚቀርብ የማብራሪያ ጥያቄም ሆነ ለጥያቄው የሚሰጥ መልስ በሁሉም ተጫራቾች እንዲታወቅ ሆኖ በጽሑፍ መሆን አለበት::

4. በጨረታው አሸናፊ የመወዳደሪያ ሃሳብ ውስጥ የቀረበው ዋጋ፣ጨረታው ከመውጣቱ በፊት በግዥ ፈፃሚ አካል ከተገመተው ወጪ በከፍተኛ ልዩነት የሚበልጥ ከሆነ የግዥ ፈፃሚው አካል ወጪው ከታሰበው በላይ የሆነበትን ምክንያት ማጣራት እና አዲስ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣት ያስፈልግ እንደሆነ መመርመር አለበት::

## 32. ጨረታ የሚቆይበት አነስተኛ ጊዜ እና ድጋሚ ጨረታ ስለ ማውጣት

1. የግዥ ፈፃሚ አካል የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ የሚቀርብበትን የመጨረሻ ቀን ይወስናል:: ይሁን እንጂ ጨረታ የሚቆይበት አነስተኛ ጊዜ፣

   ሀ. ለአገር ውስጥ ግዥ 30 ቀናት፣

   ለ. ለዓለም አቀፍ ግዥ 45 ቀናት፣

   መሆን አለበት::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀስ 1 የተመለከተው ቢኖርም ግዥው የሚፈፀመው በውስን ጨረታ ሆኖ የተጋበዙት ተጫራቾች በሙሉ ከጊዜ ገደቡ በፊት የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን ካቀረቡ የጊዜ ገደቡ እስከ ሚጠናቀቅ መጠበቅ ሳያስፈልግ ግዥ ፈፃሚው አካል ተጫራቾችን በማሳወቅ የጨረታው ሰነድ እንዲከፈት ሊያደርግ ይችላል::

3. ድጋሚ ጨረታ ማውጣት የሚያስፈልገው፣

   ሀ. የጨረታው ሰነድ በግዥ ፈፃሚው አካል የሚፈለገውን መሠረታዊ ጉዳይ ያላካተተ መሆኑ ሲታወቅ፣

   ለ. በጨረታው ሰነድ የቀረበው ዋጋ ተወዳዳሪ የገበያ ዋጋ አለ መሆኑ ሲታወቅ፣

   ሐ. የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆንና ይኸው ተጫራች በብቸኝነት እንዲቀርብ ያስቻለው በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ የተዘረጉትን ሥርዓቶች ያልጠበቀ አሠራር /ሁኔታ/ መኖሩ ሲረጋገጥ፣

4. ጨረታውን ያወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል የቀረበው አንድ ተጫራች የመወዳደሪያ ሃሳብ አጥጋቢ እና ዋጋውም ተወዳዳሪ የገበያ ዋጋ መሆኑን እንዲሁም የሌሎች ተወዳዳሪዎችን ተሳትፎ የሚገድቡ ምክንያቶች ያለመኖራቸውን ካረጋገጠ የቀረበውን አንድ ተጫራች አሸናፊ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 33. አቅራቢዎች አቤቱታ ለማቅረብ ስላላቸው መብት፣

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀስ 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ጨረ ታውን ያወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል በዚህ መመሪያ የተመለከተውን በአግባቡ ባለመፈፀሙ ምክንያት ጉዳት ወይም ኪሣራ ደርሶብኛል ወይም ሊደርስብኝ ይችላል የሚል ተጫራች በአዋጁ በተደነገገው መሠረት ጨረታው እንደገና እንዲታይለት አቤቱታ ማቅረብ ይች ላል፡፡

2. ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች ግን አቤቱታ ማቅረብ አይቻ ልም፡፡

   ሀ. በአዋጁ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ በተወ ሰነው የግዥ ዘዴ ምርጫ ላይ፣

   ለ. በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 11 እስከ 15 በተመለከተው መሠረት በሥራ ላይ በዋለ የተጫራቾች አመራረጥ ሥርዓት፣

   ሐ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 መሠረት ለአገር ውስጥ ምርቶች እና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች በተደረገ ልዩ አስተያየት፣

   መ. በአዋጁ አንቀጽ 23 መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሳብን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ለማድረግ በተሰጠ ውሣኔ፣

## 34. አቤቱታ የሚጣራበት ስርዓት የሚመራባቸው ደንቦች፣

1. ማንኛውም የጨረታ ግምገማ ሪፖርት ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት እንደፀደቀ ውጤቱ የጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች እና በጨረ ታው ተሳታፊ ለሆኑ ሌሎች ተጫራቾች በእኩል ጊዜ በጽሑፍ መገለጽ አለበት::

2. በጨረታው ተሸናፊ ለሆኑ ተጫራቾች የሚጻፈው ደብዳቤ የተሸነፉበትን ምክንያት እና አሸናፊ የሆነውን ተጫራች የሚገልጽ መሆን አለበት::

3. ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈፃሚ አካል የጨረታውን ወይም የቅ ሬታውን ውጤት ለተጫራቾች ከገለፀበት ቀን ጀምሮ 7 የሥራ ቀን ከመሙላቱ በፊት የግዥውን ውል መፈረም የለበትም::

4. በግዢ ፈፃሚው አካል በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ቅር የተሰኘ ማናቸውም ተጫራች ለአቤቱታው መሠረት የሆነውን ውሣኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ጨረታውን ላወጣው የግዥ ፈፀሚ አካል የበላይ ኃላፊ ሊያቀርብ ይችላል:: ከዚህ ጊዜ በኋላ ለግዥ ፈጻሚው አካል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም::

5. የግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ በአዋጁ አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 3 በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ካልሰጠ ወይም ተወዳዳሪው በግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ ውሣኔ ያልረካ እንደሆነ የግዥ ፈፃሚው አካል ውሣኔ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በአምስት የሥራ ቀን ጊዜ ውስጥ ለመንግሥት ግዥ ኤጀንሲ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል::

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ወይም 5 በተገለፀው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ጨረታውን ያወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል ወይም የግዥ ኤጀንሲው አቤቱታ መቀበል አይኖርባቸውም::

7. አቤቱታውን ባቀረበው ተጫራች እና ጨረታውን ባወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል በስምምነት ካልተፈታ በስተቀር እንደአግባብነቱ ጨረ ታውን ያወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል ወይም የግዥ ኤጀንሲ አቤቱታው በቀረበ በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን በፅሑፍ መስ ጠት አለበት::

8. አቤቱታውን የሚያጣራው የግዥ ኤጀንሲ ከሆነ ግዢ ፈፃሚው አካል አቤቱታውን ለማጣራት የሚያስፈልጉትን መረጃዎች እንዲያቀርብለት በግዥ ኤጀንሲው ጥያቄ በቀረበለት በ5 ቀን ጊዜ ውስጥ ተፈላጊዎቹን መረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል::

9. ጨረታውን ያወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል ወይም የግዥ ኤጀንሲ በቀረበው አቤቱታ ላይ የሰጧቸው ውሳኔዎች ግልባጮች ውሳኔ በተሰጠ በ5 ቀናት ውስጥ እንደአግባብነቱ አቤቱታውን ላቀረበው ተጫራች እና ወይም ጨረታውን ላወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል እንዲደርሱ መደረግ አለበት:: በተጨማሪም የተሰጠው ውሳኔ ለሕዝብ ክፍት መደረግ አለበት::

10. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተጫራቾች የቴክኒክና የዋጋ ማወዳዳሪያ ሃሳባቸውን በተለያየ ኢንቨሎፕ እንዲያቀርቡ በተደረገበት ጨረታ፣ በቴክኒክ የመወዳደሪያ ሃሳቡ ግምገማ ተፈላጊውን ነጥብ ባለማግኘቱ ከጨረታ ውጪ የተደረገ ተጫራች

የተጫራቾች የዋጋ መወዳደሪያ ሀሳብ ከመከፈቱ በፊት አቤቱታውን ለግዥ ፈፃሚው አካል ሊያቀርብ ይችላል። ባቀረበው አቤቱታ ላይ በግዥ ፈፃሚው አካል በተሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ተጫራች ለግዥ ኤጀንሲ አቤቱታውን ማቅረብ የሚችለው የጨረታው ግምገማ ተጠናቆ አሸናፊው ከታወቀ በኋላ ይሆናል።

11. የተሰጠው ውሣኔ ለሕዝብ ክፍት መደረጉ ከሕግ ተቃራኒ ከሆነ፣ የሕግን አፈፃፀም የሚያሰናክል፣ የሕዝብን ጥቅም ያልጠበቀ፣የተሳታፊዎችን የንግድ ጥቅም የሚጎዳ ወይም ውድድርን የሚያደናቅፍ ከሆነ ለሕዝብ ክፍት መሆን የለበትም።

12. አቤቱታ የቀረበበት ማናቸውም ግዢ የሚጣራው ለጨረታ በቀረበው ዋንኛ ሠነድ መሠረት ይሆናል።

## 35. የግዥ አፈፃፀም ሒደትን ስለማገድ፣

1. አቤቱታው ፍሬ ነገር ያለው እና የያዘው መግለጫ እውነት መሆኑ ከተረጋገጠ፣እንዲሁም የዕገዳው ውሣኔ መተላለፍ ጨረታ ያወጣውን ግዥ ፈፃሚ አካል እና የሌሎችን አቅራቢዎች ጥቅም የማይጎዳ ሲሆን ከዚህ በላይ በአንቀጽ 32 በተመለከተው መሠረት በተገቢው ጊዜ ውስጥ የቀረበው አቤቱታ ውሣኔ እስከሚያገኝ ድረስ ጨረታው ታግዶ እንዲቆይ መደረግን ያስከትላል።

2. የግዥው ውል ከተፈረመ በኋላ ክብደት የሚሰጠው አቤቱታ የቀረበ ሲሆን እና ይህም አቤቱታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ጨረታውን ያወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል ጉዳዩ ውሣኔ እስከሚያገኝ ድረስ የግዥው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል።

3. ጨረታውን ያወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል በአስቸኳይ መሟላት ያለበትን የመንግሥት ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግዥው አፈፃፀም መቀጠል እንደሚገባው ካረጋገጠ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተው ዕገዳ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

4. የግዥው አፈፃፀም ሥርዓት ቃለ-ጉባዔ አካል የሚሆነው እና ግዥው በአስቸኳይ መፈፀም ያለበት መሆኑ የታወቀበትን ምክንያት የሚገልፀው ማረጋገጫ በፍርድ ቤት ካልሆነ በስተቀር በሌሎች በዚህ መመሪያ አቤቱታ እንደሚሰሙ በተመለከተው አካላት እንደገና ሊታይ አይችልም፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 መሠረት በግዥ ፈፃሚ አካላት የሚተላለፍ ማናቸውም ውሣኔ እንዲሁም የውሣኔው ምክንያቶች እና ሁኔታዎች የግዥውን ሥርዓት የሚያሳዩ ሰነዶች አካል ሆነው መመዝገብ አለባቸው፡፡

## 36. አቤቱታን በፍርድ ቤት ስለማየት፣

ጨረታውን ባወጣው የግዥ ፈፃሚ አካል ወይም በመንግሥት ግዥ ኤጀንሲ ውሣኔ ቅር የተሰኘ ተጫራች ጉዳዩን አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 37. የተሻሩ መመሪያዎች፣

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የግዢ መመሪያ ቁጥር 1/1991 ከነማሻሻያዎቹ ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

## 38. የሚፀናበት ቀን

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

**ሱፍያን አህመድ**

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር

## የጨረታ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኃላፊነቶች

የጨረታ ኰሚቴው ሰብሳቢ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚሾም ሆኖ የሚከተ ሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. የጨረታ ኰሚቴውን ስብሰባ ይመራል፡፡

2. በጨረታ መዝጊያ ዕለት ተገኝቶ የጨረታ ሣጥኑን ያሽጋል፡፡

3. በጨረታው መክፈቻ ቀን ተገኝቶ፣ ጨረታ ከመከፈቱ በፊት መሟላት ያለባቸው ደንቦች እና ሥነ-ሥርዓቶች መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፡፡

4. ተጫራቾች እና የጨረታ ኰሚቴ አባላት በተገኙበት የጨረታው ሣጥን በሚገባ መታሸጉን ያሳያል፣ ሣጥኑ እንዲከፈት ያደርጋል፡፡

5. የጨረታው መክፈቻ፣ የስብሰባው ሂደቶች እና በግምገማው የተደ ረሰበት ውሣኔ በሚገባ በቃለ-ጉባዔ መመዝገባቸውን እንዲሁም የተ መዘገበው ቃለ-ጉባዔ ተሟልቶ መቅረቡን ያረጋግጣል፡፡

6. የጨረታ ኰሚቴው የውሣኔ ሃሳቦች በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንዲ ፀድቁ ያቀርባል፡፡

# የጨረታ ኰሚቴ ፀሐፊ ኃላፊነቶች

የጨረታ ኰሚቴ ፀሐፊ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚሾም ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነ ቶች ይኖሩታል፡፡

1. ማንኛውንም የጨረታ ኰሚቴውን የስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ይመዘግባል፣ ኰሚ ቴው የተሟሉ ሠነዶች እና መዛግብቶች እንዲኖሩት ያደርጋል፣ በጥንቃቄ ይይዛል፡፡

2. በጨረታ አፈፃፀም ሂደት ከአቅራቢዎች ጋር የተደረገ ውይይት ካለ በቃለ ጉባዔ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

3. የጨረታ ኰሚቴው መቼ እና የት እንደሚሰበሰብ ለውስጥ ኦዲት ይገልፃል፡፡

4. ለሚካሄደው ጨረታ አስተማማኝ የጨረታ ሳጥን እንዲኖር ያደርጋል፣ የጨ ረታ ሣጥኑ በትክክል መቆለፉን አረጋግጦ መክፈቻውን በጥንቃቄ ይይዛል፡፡

5. በጨረታ ሣጥኑ ውስጥ ሊቀመጡ የማይችሉ ሠነዶችንና ናሙናዎችን ፈርሞ ይቀበላል፡፡ ሠነዶቹንና ናሙናዎቹን በሚስጥር ይይዛል፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለጨረታ ኰሚቴው ያቀርባል፡፡

6. በጨረታው መዝጊያ ቀን ከኰሚቴው ሰብሳቢ እና አባላት ጋር በመሆን የጨረታውን ሣጥን ያሽጋል፡፡

7. የጨረታ መወዳደሪያ ዋጋ ሠንጠረዥ እንደአስፈላጊነቱ ያዘጋጃል፣ በቃለ-ጉባዔ በተመዘገበው መሠረት ትክክለኛው የመወዳደሪያ ዋጋ በሠንጠረዥ ውስጥ መካተቱን ያረጋግጣል፡፡

8. ከኰሚቴው ሰብሳቢ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት አጀንዳ ያዘጋጃል፡፡

9. ከጨረታው የጊዜ ገደብ በኋላ የደረሱ የጨረታ ሠነዶች ሳይከፈቱ ለላኪው እንዲመለሱ ያደርጋል፡፡

10. በጨረታ ኮሚቴ ስብሰባዎች ድምፅ ይሰጣል፡፡

# ማ ው ጫ


| ተራ ቁጥር | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 | አጭር ርዕስ | 1 |
| 2 | ትርጓሜ | 1 |
| 3 | የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን | 2 |
| 4 | መርሆዎች | 2 |
| 5 | የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች | 4 |
| 6 | በውሱን ጨረታ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለበት | 4 |
| 7 | በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለበት | 5 |
| 8 | ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለበት | 5 |
| 9 | ልዩ ሁኔታዎች | 6 |
| 10 | በተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች ግዥ ለመፈጸም በቅደም ተከተል መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች | 7 |
| | ◆ የጨረታ ጥሪ | 7 |
| | ◆ በጨረታ ለመሳተፍ ብቃት ያላቸውን መምረጥ | 9 |
| | ◆ የጨረታ ሠነድ | 9 |
| | ◆ የተጫራቾች መመሪያ | 9 |
| | ◆ የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር ( Specification) | 13 |
| | ◆ የጨረታ ሃሳብ ማቅረቢያና የዋጋ ሠንጠረዥ | 15 |
| | ◆ የውል ሁኔታዎች | 16 |
| | ◆ በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ | 17 |
| | ◆ የጨረታ አከፋፈት | 17 |
| | ◆ ከጨረታ ውጪ ስለማድረግ | 18 |
| | ◆ ጨረታን ስለመመርመር | 19 |
| | ◆ ጨረታን ስለመገምገምና ስለማወዳደር | 20 |
| | ◆ የጨረታ ማስከበሪያ | 22 |
| | ◆ የውል ማስከበሪያ | 23 |
| 11 | በሁለት ደረጃ የሚፈጸም ግዥ | 25 |
| 12 | የመወዳደሪያ ሃሳብ በመጠየቅ የሚፈጸም ግዥ | 25 |
| 13 | ውስን ጨረታ | 25 |
| 14 | በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ | 26 |
| 15 | ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ | 27 |
| 16 | ዓለም አቀፍ ጨረታ | 27 |
| 17 | የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚደረግ ግምገማና ውድድር | 28 |
| 18 | የምክር አገልግሎት | 28 |
| 19 | በጥራትና በዋጋ ላይ የተመሰረተ መረጣ | 28 |
| 20 | በሚከናወነው ሥራ ጥራት ላይ የተመሰረተ መረጣ | 30 |
| 21 | በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ | 30 |
| 22 | በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሰረተ መረጣ | 31 |
| 23 | ሌሎች አገልግሎቶች | 31 |
| 24 | የግዥ ፈጻሚ አካል ኃላፊነት እና ስልጣን | 32 |
| 25 | የጨረታ ኮሚቴ አሰያየም | 32 |
| 26 | የጨረታ ኮሚቴ ኃላፊነት | 33 |
| 27 | ተቀባይነት ባገኘ የአቅራቢዎች ዝርዝር ስለመጠቀም | 35 |
| 28 | ከግዥ ፈጻሚ አካላት የሚቀርቡ መደበኛ ያልሆኑ የግዥ ሃሰቦችን ስለመመርመር | 39 |
| 29 | የተሸከርካሪ ግዥ አፈጻጸም | 39 |
| 30 | የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ክፍያ የምስክር ወረቀት | 40 |
| 31 | ለግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ግዥ አፈፃፀም ስለሚደረግ የቴክኒክ ድጋፍ | 42 |
| 32 | የቅድሚያ ክፍያ | 42 |
| 33 | ልዩ አስተያየት | 44 |
| 34 | የሙያ ስነ-ምግባር | 45 |
| 35 | ከአቅራቢዎች ጋር ስለሚደረግ ውይይት | 46 |
| 36 | ጨረታ የሚቆይበት አንስተኛ ጊዜ እና ድጋሚ ጨረታ ስለማውጣት | 48 |
| 37 | አቅራቢዎች አቤቱታ ለማቅረብ ስላላቸው መብት | 49 |
| 38 | አቤቱታ የሚጣራበት ስርዓት የሚመራባቸው ደንቦች | 50 |
| 39 | የግዥ አፈጻጸም ሒደትን ስለማገድ | 52 |
| 40 | አቤቱታን በፍርድ ቤት ስለማየት | 53 |
| 41 | የተሻሩ መመሪያዎች | 53 |
| 42 | የጨረታ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኃላፊነቶች ዕዝል | 1 |
| 43 | የጨረታ ኮሚቴ ፀሐፊ ኃላፊነቶች ዕዝል | 2 |